**አርቲክል**

**በሳሮን ስማቸው**

# *ታሪክ ቀያሪው......*

**በብዙ የፖለቲካና የታሪክ ሽፍጦች ተተብትቦ ከኖረው ወንዛችን የተገኘው ሰው ሰራሽ ፀጋ ሲዳሰስ**

*የአባይ እድሜው ስንት ነው? ለስንት አመታት ውጭ ናፋቂ፣አገሩን ጠል፣የሌላ ሲሳይ ሰጭ ሆኖ ኖረ?... አንድ ሺህ... አምስት ሺህ...አንድ ሚሊዮን አመታት... እኔ እድሜ ግመታው ላይ የለሁበትም፤ገና የ35 አመት እድሜ ያለኝ አንድ ፍሬ ልጅ ስለሆንኩ... ይለፈኝ፡፡*

*አይ አባይ! ለዘመናት ገጣሚዎቻችን፣ ባለቅኔዎቻችን እና ዘፋኞቻችን ቀጥተኛም ይሁን አሽሙር ስድብንና ዘለፋን አውርደውብህ የዝሆን ጆሮ እና ወፍራም ቆዳ ተሰጥቶህ! ምንም ትንፍሽ ሳትል ያለማንም ከልካይ ዝም ብለህ መሄድ... መሄድ...ዝም ብለህ መፍሰስ.. ዝም ብለህ ወደ ውጭ መጋለብ..፡፡ እውነት ግን በውሃ ጥም የሚሰቃዩ፣የሚሞቱ ኢትዮጵያዊ ወገኖችህ መኖራቸውን ዘንግተህ ነው? ወይስ የራሳቸው ጉዳይ በሚል ግዴለሽነት? በረሀብ የሚሰቃዩትና የሚሞቱትስ? ይህ እጅግ የከፋው በወንጀል የሚያስጠይቅህ ግፍ ቢሆንም ሀገር ሙሉ ለም አፈራችንን ተሸክመህ ምን ታመጣላችሁ በሚል ትዕቢት አሁን ድረስ መሄድህን አላቆምክም፡፡ በዚህ የአባይ እኩይ ድርጊት የተናደደ በአለማዊ ስሙ ኃይሉ ገብረዮሀንስ በብዕር ስሙ ደግሞ “ገሞራው” የሚባል ገጣሚ እና ባለቅኔ እጅግ ሰዋዊ በሆነ አተራረክ አባይን ከእነ ወላጁ እንዲህ ሲል ይሰድበዋል፡፡*

*ይፈሳል ይሉኛል፣ አባይ ዐይኑ ይፍሰስ፣*
*ያን ስንቱን ወገኔን የውሃ እጦት ሲያምስ፣*
*የድርቀት ጋንጩራ ሲበላ ስንቱን ነፍስ፣*
*ውሃ ውሃ እያለ ለጋው ሲቀነጠስ፣*
*ናይል አባያችን . አለ ነበር ሲፈስ፡፡*
*ለፈፀመው ደባ ለሰራውም ግፉ፣*
*«እናትክን!» በሉልኝ በዚያ የምታልፉ፡፡*

*እርግጥ ነው “ገሞራው” አባይን እስከ እናቱ መስደቡ አግባብ ነው... እሱማ ግዑዝ አይደል ሀገሩ ነበረች እንጅ ማልማት የነበረባት... ሰው ሀገር ናትና.. ሀገርም ሰው ናትና፡፡*
*ያሬድ ዘጨጎዴ የተባሉ ታላቅ ባለቅኔም አባይን.. በመዝባሪነቱና በክፉ ወላጅ አስለቃሽነቱ፣ወላጅን አሳዛኝ፣ እንባ አራጭ የሌባ፣የዘራፊ ተምሳሌት እንደሆነ እንደሆነም... ባለቅኔው እንዲህ ብለውታል፡፡*

ፅሩዕ ምግባረ ግዮን ልቡናሃ ለኢትጵያ አንደደ

አምጣነ ቤታ ከረየ ወንዋያቲሃ ወሰደ።

በማለት በግዕዝ ተመሳጥረዋል። ትርጉሙም፡—

ምግባረ ብልሹ አባይ የኢትዮጵያን ልብ አሳዘነ

ቤቷን በርብሮ ንብረቶቿን ወስዷልና። ማለት ነው።

እንደተመላከተው የአለም ሎሬት የሆኑት የእኛው ባለቅኔ ጋሽ ጸጋዮ ገብረመድህንም "እሳት ወይ አበባ" የሚል መጠሪያ ባለው የግጥም መድብል መጽሀፋቸው አባይ የስልጣኔ ምንጭነቱን፣ ውበት ሀብቱን፣ ቅርስነቱን፣የኩራት ምንጭነቱን፣ ወዘተ. በውብ ቋንቋ እንዲህ ሲል አወድሶታል።

አባይ የምድረ ዓለም ሲሳይ፣
የቅድመ-ጠቢባን አዋይ፣
አባይ የጥቁር ዘር ብስራት፣
የኢትዮጵያ ደም እናት።
የዓለም ስልጣኔ ምስማክ፣
ከጣና በር እስከ ካርናክ፣
በእቅፍሽ ውስጥ እንዲላክ።

"አድኖ መግደል" በሚባለው ዘይቤያዊ አገላለጽ አባይ ለኢትዮድያ ስም ብቻ እንጅ ምንም እንዳልጠቀማት፣አባይን ያህል በአለም ረጅሙን ስመ ገናና ወንዝ እያላት ስሟ በረሀብ የምትጠራ አገር ያደረጋት ከንቱ ወንዝ መሆኑን በዚህ መልኩ ወርፎታል።

በመመለክ በመመስገን፣
ጽላትሽ ከዘምን ዘመን፣
በአዝዕርትሽ አበቅቴሽ ሲታጠን፣
አቤት አባይ ላንቺ መገን።

አይ አባይ! ያላቃጠለው ሰው እኮ የለም። እጅጋየሁ ሽባባው ወይም በቅፅል ስሟ "ጅጅ" ብለን የምንጠራት ተወዳጇ ድምፃዊ እጅግ ውስጥን በሚያሳምም ስሜት.. እንዴት ለእነሱ ብቻ ሆንክ በሚል ቁጭት፣ የበረሐ ሞገስ ብቻ ሆንክ.. ለምን ተውከን እኛን" በሚል ንዴት እንዲህ በማለት አባይን ትወርፈዋለች።

ግርማ ሞገስ አባይ፣
የበረሐው ሲሳይ።

ብነካው ተነኩ አንቀጠቀጣቸው፣

መሆንህን ሳላውቅ ስጋና ደማቸው።

የሚበሉት ውሃ፣

የሚጠጡት ውሃ፣

አባይ ለጋሲ ነው በዚያ በበረሃ።

ወዘተ.¸ወዘተ. እና ሌሎችም ዘፋኞቻችን፣ገጣሚዎቻችን እና ባለቅኔዋቻችን አባይን በአብዛኛው በአሉታዊ መልኩ ሲወቅሱት በጥቂቱ ደግሞ በአወንታዊ ሲያሞግሱት በርካታ አመታት አልፈዋል። "መሰንበት ጥሩ ነው..." እንደሚባለው ያን የውግዘት ታሪክ የሚቀይር አንድ ትልቅ ጉዳይ በአባይ ወንዝ ላይ እውን ሊሆን መጋቢት 24/ 2003 ዓ.ም ላይ በአለም አስተጋባ... "ኢትዮጵያ አባይን ልትገድብ የመሰረት ድንጋይ አስቀመጠች" የሚል። በዚህ ክስተት ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ተንፀባረቁ–ደስታና ሀዘን። ኢትዮጵያውያን ደስታቸው ሲበዛ ግብፆች በድንጋጤና በሀዘን እንዲዋጡ ሆኗል። ታሪክ ቀያሪው አባይን የመገደብ ወሳኝ ፕሮጀክት በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ከተጀመረበት እለት አንስቶ "ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ላለፉት 14 ድፍን አመታት ሲገነባ ኖሮ በመጠናቀቁ ጳጉሜ 4/2017 ዓ.ም በወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አብሳሪነት የተለያዩ ሀገራት መሪዎች እና የዓለም አቀፍ ተቋማት ሃላፊዎች በተገኙበት ሥነ ሥርዓት ተመርቋል። ግድቡ በትልቅነቱ በአፍሪካ አንደኛ በአለም ደግሞ 10ኛ ደረጃን ይዞ ይገኛል። እንደተዘገበው ግድቡ አምስት ሺህ 150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ሲኖረው የግድቡ የውሃ የመያዝ አቅም 74 ቢሊዮን ኪውቢክ ሊትር ውሃ ነው። የግድቡ ከፍታ ርዝመት 145 ሜትር ሲሆን የግድቡ የጎን ርዝመት አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር መሆኑን ታውቋል። በግድቡ ምክንያት የተፈጠረው ሀይቅ "ንጋት" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ከ80 በላይ ደሴቶችን ፈጥሯል።

"ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ" እንደ ስሙ ታላላቅ የታሪክ እጥፋቶችን አድሷል። ይህ ትውልድ የአባቶቹን ታሪካዊ አደራ አክብሮ መፈፀም መቻሉን የታየበት ግድብ ነው። የቅኝ ግዛት ዘመን የውሃ ውል ይዘው 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ለሚያላዝኑ ቁሞ ቀር ታሪካዊ ጠላቶታችን የአድዋው ትውልድ ዛሬ ላይም ልጆቹ ተተክተው አገርን የማልማት ታሪክ እየሰሩ መሆኑን አሳይቷል። ግድቡ የድምፃዊዎችን የዜማ ቅኝት፣የገጣሚዎቻችንና የባለቅኔዎቻችን የአፍራሽ ወይም አሉታዊ እይታ ወደ አወንታዊ ስሜት እንዲቃኝ አድርጓል። ለኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ትልቅ መሰረት የጣለ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ነው። ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወደሱ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በራሷ

የፋይናንስ አቅም፣ በራሷ መሀንዲሶች መንንባት እንደምትችል  ምስክር ሆኗል…ወዘተ.ወዘተ.

በመጨረሻም የዚህ ዘመን ትውልድ ትላልቅ አገራዊ ስራዎችን ማሳካት የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም እንዳለው አሳይቷል። ለዚህ መገለጫ የሆነውን አሻራ በህዳሴ ግድቡ ላይ አስቀምጧል። ይህ በእውነቱ ታሪካዊ እድልና ድል ነው። በቀጣይም አገራችን አስተማማኝ ሰላም አግኝታ በአዲሱ አመት ሌሎች ግዙፍ የልማት ድሎችን የምናስመዘግብ ትውልዶች እንድንሆን እየተመኘሁ ተሰናበትኩ - ሰላም!

(ምንጭ፡- EGYPT-@ዘሪሁን አበበ ብሎግ- zenileabay.worldpress.com፣ኢትዮ ነጋሪ ብሎግ)